ቀደም ሲል በኦሪት ሥርዓት በተገለጸው መሠረት፣ በዚያን ዘመን ሕፃናት ሴቶች በሰማንያ ቀን፣ ሕፃናት ወንዶች ደግሞ በተወለዱ በአርባ ቀን በቤተ ሰቦቻቸው አማካኝነት በቤተ መቅደስ በመገኘት በካህን መባዕ ይቀርብላቸውና ይባረኩ ነበር (ዘሌዋ.፲፪፥፩–፰)። ከማንኛውም ኃጢአት ንጹሕ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ፣ የኦሪቱን ሕግ ለመፈጸም ሲል በተወለደ በአርባ ቀኑ እናቱ ወደ ቤተ መቅደስ ወስዳው መሥዋዕት ቀርቦለታል። አረጋዊው ስምዖንም ተቀብሎ እንዲታቀፈው ፈቅዶለታል (ሉቃ. ፪፥፳፰)።


## ቃለ ምዕዳን

ከአባ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ

ዋሽንግተን ዲሲ – አሜሪካ


የካቲት ፲፱፻፺፮ ዓ.ም